# The Ethiopian Millennium የኢትዮጵያ 2ሺ

Volume 1, Issue 1

July 2007

**Special points of interest:**

- Abby Lakew will be the main performer at the Ethiopian Millennium celebration in San Diego
- Ethiopian Millennium in San Diego will be celebrated on Sep 8, 2007
- The Millennium Ethiopian Idol is accepting audition for starting from July 1, 2007
- Volunteers are wanted for the millennium celebration

**Inside this issue:**

| | |
|---|---|
| የኢትዮጵያ 2ሺ አመት | 1 |
| ኑሮ በአሜሪካ | 1 |
| ታሪክ | 4 |
| ያሳደግሁት ግመል ነከሰኝ | 8 |
| ለመዝናኛ | 8 |
| ርእስ አንቀጽ | 3 |
| እስኪጣራ ማን ይጉላላል? | 4 |

## የኢትዮጵያ 2ሺ አመት (ሚሊኒየም) ታሪከዊ ዕለቶቹ በአጭሩ

### የኢትዮጵያ 2ሺ አመት (ሚሊኒየም) ታሪከዊ ዕለቶቹ በአጭሩ

### መግቢያ

ኢትዮጵያ በአለማችን ከሚገኙ አገሮች ሁሉ በብዙ መልኩ የተለየች ጥንታዊትና የታሪክ ማህደር ነች:: ይኸውም

በታሪክ ተ ማራማሪዎችና ፀሀፊ ዎች፤በቅዱሳን መጽሐፍት በአንትሮፖሊጂስቶች በአርክሎጂስቶች ወ.ዘ.ተ ዘንድ ከፍተኛ አስተዎጾኦ ያበረከተች ከመሆኗም በላይ የራሷ የሆነ አሃዝ ወይም ቁጥር፤የዘመን አቆጣጠር ያላትና እኛ ብቻ ሳንሆን መላ የአፍሪከ ህዝቦች ጭምር የሚኮራበት የጽሁፍ ፊደል ባለቤት መሆኗ የአለም ህዝብ ሁለተናዊ የስልጣኔና የታሪክ ማህደር እምብርት አድርጓታል::

የኢትጵያን ጥንታዊ የባህል ታሪ ክ ክምችት ማዕ ከላዊነት የሚገልፁ ከብዙ ጥቂቶችን ለአብነት ለመግለፅ ያህል:

1\. ዛሬ በአለም ቅርስነት ተመዝግበ ከሚገኙት አያሌ የኢትዮጵያ የኪነ-ጥበብ ውጤት ከሆኑት ታሪከዊ አርክተክቸሮች አንዱ የሆነው በቀድሞ የንግስት ሳባ መዲና (ዋና ከተማ) አክሱም ላይ በ4ኛ ክፍለ-ዐለም (B.C) የተገነቡ የአክሱም ሀውልቶች

2ኛው ገፅ ዞሯል

## ኑሮ በአሜሪካ

### ይድረስ ለወንድም ጋሼ

የኢብራሂም ኑሩ ገጠመኝ

ወንድሜ ሆይ እስቲ ኑሮህን ፃፍልኝ ያልከኝን አስቤ ባጭሩ ይህንን የአሜሪካን ገፅታ ላሳይህ ወደድሁ ስለምንስ እኔ ያየሁትን አንተም ብታየው ለልጆቹ ብታሳውቃቸው ብየ:: ይህም እኮ ት/ርት ነው::

7ኛው ገፅ ዞሯል



**Ethiopian Millennium Organizing committee members**

Bekele Geleta
Derege Abebe
Ibrahim Nuru
Ezana Tamirat
Mekonen Gebru
Wondosen Cherinet
Gizaw Mamo
Moges WeldeYohaness
Amde Mitiku
Hailemeskel Koricha

The Ethiopian Millennium Monthly magazine published by Ethiopian Millennium Organizing Committee

**የኢትዮጵያ 2ሺ**

ወርሃዊ መፅሔት
በኢትዮጵያ 2ሺህ
ባህል አከባበር
አስተባባሪ
ኮሚቴ እየተዘጋጀ
የሚወጣ
ወራሂ መፅሔት

# የኢትዮጵያ 2ሺ አመት (ሚሊኒየም) ታሪከዊ ዕለቶቹ በአጭሩ

ከ 1ኛው ገፅ የዞረ

2. ኢትዮጵያ የአለም ህዝብ በዘላንነት ያለማዕከላዊ መንግስት ይኖር በነበረበት ወቅት ማዕከላዊ መንግስትን መሰረት ያደረገ የአስተዳደር ስርአት ገንብታ ከህንድ፤ከሮማ፤ከቻይናና ከግሪክ ጋር የዛሬ ስልጣኔ መሰረት የሆነ የንግድ ልውውጥ ማእከል በመሆኗ

...3 አትዮጵያ ከመፅሀፍ ቅዱስ ሀገሮች አንዷና ቀደምት ሀገር መሆኗ

4 .ኢትዮጵያ የሰው ዘር መገኛና ጥንታዊት መኖሪያ ማእከል መሆኗ

5 ኢትዮጵያ የጥንታዊ የሙሴ ጽላት ( Arc of Covenant) ማደሪያ በመሆኗ

6 .የአለም ስልጣኔ ምንጭ የሆነ የአባይ ወንዝ (Nile River Civilization) መነሻ (መፈጠሪያ) ሀገር በመሆኗ

7. ኢትዮጵያ የአለም ድንቅና ብርቅዬ አትሌቶች ሀገር መሆኗና ሌሎች በአንድነት ላይ የተመሰረተ የብሄር ብሄረሰቦቿ ህብር ጥምረት ወይም ተስስር ዛሬ በታሪክ አጋጣሚ እድል ያገኙ ትውልዶች 2ሺ ዓመት አውደ በዓሉ ለመቀበልና ለማክበር እንዲኮሩ አድርጓቸዋል::

## ሚሊኒየም ምንድን ነው?

ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከርነው በርከታና ሁሉን አቀፍ ታሪኮች ውስጥ የጽሁፍ ፊደላችን፤አሃዛችን (ቁጥራ ችን) እና የዘመን አቆጣጠራችን የሚመለከት ይህን ጽሁፍ የረጅም ዘመን እድሜ ስለአለው የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ውጤት ስለሆነው የጁሊያን (Julian) ዘመን 2ሺ ዓመት በዓል አከባበር ነው::

እንደሚታወቀው የዛሬ ሰባት አመት ገደማ ፈረንጆች በዘመን አቆጣጠር ቀመራቸው (በግሪጎሪያን ዘመን አቆጣጠር) የሺ አመት በአላቸውን በእነሱ አጠራር ሚሌኒየም (Millennium) የሚሉት አክብ ረዋል::

ኢትዮጵያችንም አርባ አምስት (45) ቀናት በኋላ የዚያኑ አይነት አውደ-በአል በከፍተኛ ስሜትና ድምቀት ለመቀበልና ለማክበር እየተዘጋጀች መሆኗ ይታወቃል:: ይህንን <u>አውደ በአል</u>

...ኢትዮጵያችንም አርባ አምስት (45) ቀናት በኋላ የዚያኑ አይነት አውደ-በአል በከፍተኛ ስሜትና ድምቀት ለመቀበልና ለማክበር እየተዘጋጀች መሆኗ ይታወቃል:: ይህንን <u>አውደ በአል</u> በትውልድ ተርታችን አጋጣሚ የደረስንበት ኢትዮጵያውያን ሁሉ በምስጋናና በፍስሃ ልንቀበለው ይገባናል:: የዚህ አይነቱን <u>የሺ አመት ክብረ-በአል በህይወት ኖረው ለማየት</u> የሚበቁት ከብዙሃን ያለው ዘሮች መከከል ጥቂቶቹ መሆናቸው ግልፅ ነው:: እነሆ ይህ ብቸኛ የኢትዮጵያ ሺ አመት አቀባበልና አከባበር መርሃ ግብር ወጥቶ በመንግስትም፤በህዝብም እና በግለሰቦችም ደረጃ ጉዳዩ አትክሮት እያገኘ፤ እየታሰበበትና እየተመከረበት ባለበት ባሁኑ ግዜ በአሉን በሚሌኒየም ስም ብቻ ላለማክበር እና የአሁኑ ትውልድም የሚሌኒየምን የፈረንጆች ቃል በራሱ ቋንቋ ተርጉሞ ማወቅ ስለአለበት

2ኛው ገፅ ዞሯል

**AWASH MARKET**

**አዋሽ ገበያ**

The Ethiopian Market Store

injera, phone card, fresh beef,

Importing Ethiopian made spices.

Ethiopian beer and wine

ለሰርግ፣ ለልድት ለሌሎችም ባእላት ዳቦ በትዛዝ እናዘጋጃለን፡፡በሀገር ቤት የተቀመሙ የቅቤ ማንጠሪያ፣ የወጥ እና የሌሎችንም ቅመማ ቅመማት እናዘጋጃለን በጅምላ እናከፋፍላለን፡፡

619) 282-8280

2876 El Cajon Blvd,

San Diego, CA 92116

Design by www.yebbo.com

# ርእስ አንቀጽ



(ይህ ርእስ አንቀጽ የአዘጋጅ ኮሚቶዎቹ አቋም የሚንፀባረቅበት ክፍል ሲሆን እምነታችንና ስራችንን እዚህ እናሰፍራለን)

የ13 ወራት ባለቤት የሆነችው ሀገራችን ኢትዮጵያ ለ 2000 ዓመታት ከከበረች በኃላ አዲስ ሚሊኒየም ለመቀበል ደፋ ቀና እያለች ነው:: በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትየጵያዊያኖች የተ ለያዩ ኮሚቲዎች በማዋቀር በዓሉን ለማክበር ሁሉም እየተ ዘጋጁ ነው:: እኛም የበኩላችንን ለማዘጋጀት እየተውተረተርን ነው:: ለመቆምም እየተጣጠርን ነው:: ደግፉን:: ወገናችን ህብረት አጥቶ ይህንን «በአንድ ሺህ ዓመት አንዴ» የተገኘን ታሪከዊ ቀን እንዲሁ እንደማናቸውም የአዘቦት ቀን ቢያሳልፉት ቁጭት ሁኖ የተሰማን ሰ ዎች ተነሳስተናል:: ህብረት የናፈቀን ጉዞውን ጀምረናል በመንገዱ፤ ምሩን፤ አሳዩን፤ ጣታችሁን ግን አትቀስሩብን:: ለልጆቻችን ኢትዮጵያዊነት ኩራት መሆኑንና ኢትዮጵያዊነትን መዝራት ነው አላማችን:: ስለ ልጆቻችን ስንል መቻቻልን እናዳብር:: ጥላቻ ጥላቻን እንጂ የሚወለድ ከጥላቻ ፍቅር አይለመልምም:: ትውልድ ከጠፋ በኃላ ለማቃናት መሞከር አሜኬላ ዘርቶ ስንዴ ለማረም ማሰብ ነው:: ያልዘሩት አይበቅልም!!

ዝግጅታችን አንዱን የተለየ የህብረተሰብ ክፍል በመወከል ወይ የአንድን የፖለቲከ ድርጅት አቋም ለማንፀባረቅ ተብሎ የተዘጋጀ ዝግጅት አይደለም:: የኛ ዝግጅት ሁሉን ብሄረሰብ ያከተተ ኢትዮጵያዊነት አለባበስ፤ኢትዮጵያ ባህል፤ የስነ ፅሁፍ ውድድር (ታለንት ሾው) ወዘተ .... ነው:: ይህ የዚህ ወይ የዚያ የሚያስብል ጉዳይ የለውም:: የኛ ዝግጅት ኢትዮጵያዊነትን ውበት አላብሶ ማቅረብ ነው:: ይህንን ዝግጅት ታዲያ ፖለቲከዊ መልክና ጭራ መስጠት ያስተዛዝባል:: ርከሽ ፖለቲከኞችም ያሰኛል:: ሁሉም በቦታው ሲሆን ያምራል::

የኮሚቲው አባላት እነማን ናችሁ? ለምትሉ እኛ ኢትዮጵያዊያን ነን:: በፖለቲከ ተ ብሎ ሰው ሲናቆር ሰናይ ልባችን የሚደማ የልዩነት መንገድ «ወዴት ይሆን የሚያመራ?» ብለን የምንጨነቅ፤ ሚሊኒየሙን በጋራ ብናሳልፈው እንዴት ያስደሰት ይሆን? ብለን የምናስብ ዜጎች ነን:: እኛ የፖለቲከ መፈክር ያንጠለጠልን ሰዎችም አይደለንም:: አላማችን በጋራ የህብረት ዜማ ለማዜም የቆምን አዲስ መንፈስ በሳንዲያጎ እንዲናኝ ይህንን የስራ ጊዜያችንን ለበጎ አላማ የዋልን ሰዎች ነን:: ታዲያ ይህ መንፈስ የሚሰማችሁ ሁላችሁም ወገኖቻችን የአቅማችሁን እንድታበረክቱ በሁሉም ኢትዮጵያውያን ስም ጥሪ ያችንን እናቀርባለን:: ሁሉም በየችሎታው ቢያበረክት ለሁላችንም የሚያስደስት ነገር ይሰራል ብለን እናምናለን::


## Axum Market/አክሱም ገበያ

“በቁርጥና በክትፎ ስጋ ወደ ተመስገነው አክሱም ገበያ ብቅ ይበሉ፣ በመስተንግዷችን ይደሰታሉ!”

**በትእዛዝ በግ እናርዳለን፣ ገንዘብ ወደ ሀገር ቤት እንልካለን**

Injera, fresh beef፣ lamb፣ phone card & CD

619) 282-5339 4487 El Cajon Blvd, San Diego, CA 92115


Design by www.yebbo.com

# ታሪክ

(ይህ አምድ የኢትዮጵያ አጠቃላይ ታሪክ የሚዳሰስበት አምድ ነው:: በዚህ ክፍል አጠራጣሪ፤አከራከሪና የአንድን ወገን የበላይነት የሚያንፀባርቁ ፅሁፎች አይስተናገዱበትም::)

## ከቶ ኢትዮጵያዊ መልኩን ነብር ዥጉርጉርነቱን መቀየር ይቻ ለዋልን?

ከኢብራሂም

ኢትዮጵያ ሀገራችን የስልጣኔ ምንጭ የኩራት አለኝታ የአለም መምህር ነበረች:: የዛሬ 5.5 ሚሊኒየም ዓመታት በፊት አስትሮሎፒቲኩስ ራሚደስ (Austrolopiticus Ramids) የተ ባለው ዝንጅሮ መሰል ፍጡር በአፋር ሸለቆዎች ሲዘዋወር አለም ያኔ አልነበረም:: የኛዋ ድንቅነሽ ፈ ረንጆቹ ሉሲ ነው የሚሏት መራመድ የጀመረችው በአፋር አከባቢ ነው:: አመት አለም እንዴት ነው የደመመው በዛን ሰአት ለከ ስልጣኔ ያለው ኢትዮጵያ ኑሯል ማን አወቀ? ማን ሰማ? ሉሲ ነበረች አለምን ያሳወቀችው በሁለት እግር ቁመህ መሄድ መቻልን የዛሬ 3.5 ሚሊዮን አመት!!

ንግስት ሳባ (ስሟ ማክዳ ነው) የሀገሯ በጥበብ ጎዳና ወደኋላ መቅረት አሳስቧት የአለም በስልጣኔ መምጠቅ ቢያንገበግባት ጥበብን ፍለጋ ወደ እየሩሳሌም የሄደችው ከዚህችው የስልጣኔ ሀገር ኢትዮጵያ ነው::ምን ነበር ጥበቡ ያለው?

«እንቁ መጣሽ»

እንቁጣጣህ የሚለው በአላችን እዚህ ጋር ይጀምራል ከመልከ እኩል ብልህነቷ ወደር እንደሌለው የመሰከረው ጠቢቡ በመደመም ነው:: ዘመን ቀጥሎ ከክርስቶስ ልደት በፊት ኢትዮጵያዊው ከሌብ እስከ ደቡብ የመን ድረስ አስገብሮ ይኖር ነበር:: የመጀመሪያዋ ከተማ የ ላይ ቆርቁሮ ሊያስተዳድር እንዴት ያለ ፍትህ አዋቂ እንደነበር ይነገራል::

የቅዱስ ያሬድ ድጓ፤ፆመ ድጋ፤ አራራት እና ዜማ ዛሬ ድ ረስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤ/ክ በወረባና ሽብሸባ እግዚአብሄርን የምታመሰግንበት ነው:: የወቅቱ መሪ ገብረመስቀል በዜማው ከመመሰጡ የተነሳ ጦሩን ሲወረስ ረው ሳያውቀው የቅዱስ ያሬድን እግር መውጋቱ የዜማው ሀይለኛ ነት ያስታውቃል:: እራሱ ቅዱስ ያሬድ በዜማው ከመመሰጡ የተነሳ እግሩ ደምቶ ጭራህ አያውቀም የነበረ!!

ትውልድ ጋር ሲደርስ ምነው ወገቤን አለ? (ሳምንት ከ ንጉስ ኢዛና እንቀጥላለን)

## Ethiopian Millennium Organizing Committee Members

1. Bekele Geleta
2. Derege Abebe
3. Ibrahim Nuru
4. Ezana Tamirat
5. Mekonen Gebru
6. Wondosen Cherinet
7. Gizaw Mamo
8. Moges WeldeYohaness
9. Amde Mitiku
10. Hailemeskel Koricha

Any suggestion, comment or want to contribute ?

Write to us

Ethiopian Millennium Organizing Committee in San Diego

Address:

4535 30th St #106

San Diego, CA 92216

Email:

ethio2000sd@yahoo.com

Website:

Www.yebbo.com/ethio2000sd

### ኑሮ በአሜሪካ

ከ 1ኛው ገፅ የዞረ

*ፈረንጆቹ እንደሚሉት ት/ ርት እንደሆነ በስነ-ስርአት ት/ቤ ት ተሄዶ ድግሪ ተያዘ ተብሎና እንዲሁ በኑሮ እንዲህ በመስማት የሚማሩት ነገር መሆኑ ነው::*

*ጋሼ መጀመሪያ ያስደነቀኝ ነገር የ "Freeway" ነገር ነው::አቤት መንገድ ስፋቱና ርዝማኔው ለአይን ያማልላል:: በአንድ መንገድ ላይ 6 መኪኖች በአንድ ጊዜ ያስኬዳል ሌ ላኛው መመለሻ ሌሎች 6 መኪኖች:: የኛኑ የቀለበት መንገድ ያስታውሷታል:: የፈረንጅ ነገር እንጀራ ይውጣለት:: ትህትናው የሰው ልክ ማወቁ ህግ ማክበሩን ሳይ እኒህ መልአክ ናቸው ነው ያልኩት:: አቤት የሰው ለኩ:: እዚህ DMV የሚሉት አለ መታወቂያ የሚወጣበት አዲያ አዚያ ስሄድልህ ፈረንጁም አንደኔ ሁሉ ተኮልኩሏል::*

*...በአገሩ ከኔ እኩል ነው:: አይናደድ ሰልፍ ልስበር አይል እንደፈረደበት ቁሞ ይጠብቃል:: ያኔ እኮ አስታውሳለሁ የቀበሌ ስከር ላመጣ ሰሄድ እኔ ሁሉን አልፌ ነበር የምሄደው ምን የቆ ረጠው ያቆመኛል:: ወረፋ መጠበቅ አልወድማ! ደግሞ ምን የኀበረው ይናገረኛል ዘራፍ ... አሁን አፈርሁ ያንን ማድረጌን !*

*የፈረንጅ ጥሩነቱ አንተን ለመረዳት ያለው በጎነት ነው:: ለምን የተወላገደ እንግሊዘኛ አይሆንም ተጣጥሮ ይሰማሀል ይ ረዳሀል:: የምትለው ትርጉም የሌ ለው ነገር ቢሆን እንኳ ሊሰማህ ይሞክራል:: አሁን በቀደም "I are", "She am" እያለ የሚናገረው ቸርኬ መጥቶ ሲያወራ እኔ መሬት ተ ስንጥቃ ብትውጠኝ፤ በፍራት ይሄ ማፈሪያ አሁን ማወቁ ነው:: ደግሞ እኮ 12ኛ ክፍልን ጨርሻለሁ ይላል ቁጥር መቁጠር ሙያ ይመስል:: እሱ መሰረተ ትምህርት ነው የጨረሰው:: ኤዲያ Mr. ፈ ረንጅ እኔን ሲያሳፍረኝ ቸርኬ "I is" ሲለው "You mean I am" ሲለው "He are" እያለ ሲወላገድ "Oh, he is …" እያለ ለመረዳት ሲሞክር ሳየው አባባ ፈረንጅ ቋንቋየ ተበላሸ ሳይል መሞከሩን ሲያደንቅለት የኔው ማፈር ምን ይሉታል ብየ ኩምሽሽ አልኩ::*

*አሜሪካ ስራ አገኘህ እንጂ ምን ትሰራለህ አይሉትም:: «ያላወቁ አለቁ» ሆነና ነገሩ እኔ ወግ አገኘሁ መስሎኝ ያንን ደመቀን በቀደም ለታ አግኝቼ ጠየቅሁት ስራው ምን እንደሆነ አይ እንደው ሆድ ይፍጀው እንጂ ስራው ብር ያስገኛል «ቢል» ይከፍላል እንጂ ስራው በአማርኛ አይነግሩትም አለኝ ዘበኛ ማለትን ጠልቶት "Security" የሚለውን:: 7/11 ይላል ሱቅ ጠባቂ ማለቱን ቢጠላው የ«Gas Station» ሰራተ ኞችም ነዳጅ ማደያ ነው የምሰራው ይሉናል ልክ ጋዙን የማጣራት ስራ እንደሚሰሩ ሁሉ ! በቀደም « » የተመረቀው ደሞዜ መጥቶ በአናጢነት ተመረቅሁ አለኝ በምሬት:: አዲስ አበባ ትልቅ አስመጭና ላኪ ድርጅት አላቸው:: ነበር ምን ዋጋ አለው መሆንን አያሳይ:: ያው ተረታችን እንደሚያሳየው የትም ፍጭው ዱቄቱን አምጭው መሆኑ ነው ስራው ብር ያስገኛል!!*

*አበሾቹ ሴቶች ተቀይለረዋል ወንድም ጋሼ፤ እዛው የምትሆንህን ውሀ አጣጭህን ፈልገህ አግባ ያልከኝን ምክር አስቤ እዚህ አንገቷን የደፋች ጨዋ ብየ ሳስተ ውል ለከ ተቀይረዋል:: አቶ ባል ወጥ ይወጠውጣል ገንፎ ያገንፋል የሚሉትን ሰምቼ ያ የአቶ ዘውዱ ልጅ ምን ይውጠዋል ብዬ አሰብሁ:: አይደለም ወጥ ሊወጠውጥ እሷ የሰራችውንም አይደል ደፍቶት የሚሄደው:: ያ ኩሩ ሰው:: አቤት መጀነን እንዴት ነበር ሚያምርበት «እንደ ኩራ ሞተ እንደ ተጀነነ» እየተባለ ይገጠምለት ነበር ያኔ ድሮ ... አሁንማ ሌላ ዘፈን መጥቶ ያተረስቶ «ቢል» የምተከፍል ልምድ ያላት ይሻልሀል አለችኝ እትየ አስከለ:: ወይ «ቢል» መክፈል ምነው ልብህ የሚደነግጥላት ጠፋ .... ስለ ፍቅር መሆኑ ቀርቶ ስለ ቤት ክራይ መክፈል ሲባል ሆነ ሴቶችን የምንፈልጋቸው?*

*አማርኛችን ደግሞ እዚህ መጥተን ትንሽ ቀይረነዋል:: አሁን የተለመደው አባባል «አይ ሀሎህ» ነው:: በለመድከው ስትተረጉመው «ደግሞ ምን ታመጣ አሳይሃለሁ» እንዳይመስልህ ይህ «አይ ሃሎህ» ከእንግልዘኛው « I will see you there » ወይ ደግሞ በአማርኛ «በቃ በኋላ እንገናኛለን» መሆኑ ነው:: «አይ ሃሎህ» እሺ ወንድም ጋሼ::*

**ኑሮ በአሜሪከ፤ ገጠመኞቻችሁ፤የአሜሪከ ተሞክሮቻችሁ፤ አበሻነታችሁን፤ ኩራታችን፤ የስራ አበሳችሁን ጻፉልን እናስተናግዳችኋለን ለበለጠ መረጃ 619-253-9161**

*እኛም በዜግነታችን ብላችሁ የአገር ፍቅር ይዟችሁ የአቅማችሁን ለማበርከት ለምትሹ በሙሉ በባህላዊ አለባበስ፤በግጥም በስነፅሁፍ፤በታለንት ሾው፤ መሳተፍ የምትችሉ መሆናችሁን ለመግለፅ እንወዳለን:: ለበለጠ መረጃ:*

**ለሀይለመስቀል በ619-337-4547**

**ለኢብራሂም በ619-253-9161 ወይም ለበቀለ በ619-917-7030 ይደወሉ፡፡**

Design by www.yebbo.com

ሚሌኒየም (Millennium) ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ ትርጉሙን መስጠት አለብን:: «አባት ያለውን ልጅ ይወርሳል፤ እጅ የያዘውን አፍ ይጎርሳል» እንደሚባለው አበው ብሂል ሚሊኒየም(Millennium) = በእንግሊዘኛም ሆነ በላቲን ከሁለት የተቆራኙ ቃላት የተገኘ ቃል ነው:: እንደዚህ አይነት ጥምር ወይም ቁርኝት ቃላት ያላቸው ቋንቋዎች በእንግልዘኛ ቋንቋ Agglutinative languages ይባላሉ ስለዚህ በእንግሊዘኛ (Millennium) =(ሚል) ማለት ሺህ ሲሆን Annu (አነስ) ዓመት ማለት ነው::

በላቲን (Annus mirabilis) በእንግሊዘኛ Marvellous-Year ሲሆን ሁለቱም በአማርኛችን <u>አስደናቂ አመት</u> ማለት ነው::

ስለዚህ ይህንን የኢትዮጵያ ሁለት ሺህ አመት አስደናቂ አመት በዘመኑ ያለነው ትውልድ ለመቀበል ተቃርበናል:: እኛም በሳንዲያጎ ከተማ ነዋሪ የሆን ኢትዮጵያውያን ይህንን አስደናቂ ታላቅ አመት ክብረ-በአል አብረን ለማክበር እንዘጋጅ::

በየአመቱ መስከረም 1 ቀን በነጮች ( September 11) አዲሱን የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ቀን ቅዱስ ዩሀንስ ወይም እንቁጣጣሽ እያለ በማክበር ለሁለት ሺህ አመት የደረሰ የኢትዮጵያ ህዝብ እነሆ ዛሬ በኪነ-ጥበባት በተዋቡና በተገነቡ በረጅም ዘመን ሂደት ውስጥ በአለፉ መሰረታዊና ስርአታዊ በሆነ በተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦቿ ባህል ትስስርና ህብር የዳበረ የባህል እድገትና ማህበራዊ ግንዛቤ ውጤት የሆነውን 2ሺ አመት አውደ-በአል ለመቀበልና ለማክበር የሁሉም ኢትዮጵያዊ ትብብርና ርብርብን አሳድጎታል:: ስለዚህ ኢትዮጵያውያን ባሉበት ሁሉ ኢትዮጵያዊ ታሪክ፤ ባህልና ወግ-ማዕረግ ይኖራል:: እኛም ወደ ትውልድ ሀገራችን ሄደን በህዝባችን መሀል ተገኝተን ይህን የትውልዳችን ታላቅና አስደናቂ በዓል ማክበር ያልቻልን ኢትዮጵያውያን ባለንበት ሀገር እዚህ ሳንዲያጎ ይህን የታሪካችን ክምችት አንፀባራቂ የሆነ ታላቅ በዓል በሳንዲያጎ ከተማ ነዋሪዎች ጋር ለማክበር በዝግጅት ላይ በመሆናችን የሁሉም የሳንዲያጎ ከተማ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን ትብብርና ፈቃደኝነትን እንደማይለየን እንተማመናለን::

ከዘመኑ አበራ


# አዋሽ ምግብ ቤት

"አንዳንዴ ለደንበኛ ያቀረብነው ምግብ በትርፍ ለመግዛት ይቃጣናል"

ለልደት፣ ለቀለበት፣ ለመልስ እና ለመሳሰሉት ጉዳዮች በቅድሚያ ያስታውቁን እናዘጋጃለን፡፡

619) 583-9225

4979 El Cajon Blvd,

San Diego፣ CA 92116






## Grand Opening!

# ሀበሻ ካፌ

- ሳምቡሳ
- የቋንጣ ፍርፍር
- የበሬ ጥብስ
- ፉል

ቅዳሜ እና እሁድ ዱለት እናቀርባለን

ሀበሻ ካፌ/HABESHA CAFE

3562 Adams Ave.

San Diego, CA 92116

619 280 4223

በትውልድ ተርታችን አጋጣሚ የደረስንበት ኢትዮጵያውያን ሁሉ በምስጋናና በፍስሃ ልንቀበለው ይገባናል:: የዚህ አይነቱን የሺ አመት ክብረ-በአል በህይወት ኖረው ለማየት የሚበቁት ከብዙሃን ያለው ዘሮች መከከል ጥቂቶቹ መሆናቸው ግልፅ ነው:: እነሆ ይህ ብቸኛ የኢትዮጵያ ሺ አመት አቀባበልና አከባበር መርሃ ግብር ወጥቶ በመንግስትም፣በህዝብም እና በግለሰቦችም ደረጃ ጉዳዩ አትክሮት እያገኘ፣ እየታሰበበትና እየተመከረበት ባለበት ባሁኑ ግዜ በአሉን በሚሌኒየም ስም ብቻ ላለማክበር እና የአሁኑ ትውልድም የሚሌኒየምን የፈረንጆች ቃል በራሱ ቋንቋ ተርጉሞ ማወቅ ስለአለበት ሚሌኒየም (Millennium) ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ ትርጉሙን መስጠት አለብን:: «አባት ያለውን ልጅ ይወርሳል፣ እጅ የያዘውን አፍ ይጎርሳል» እንደሚባለው አበው ብሂል

ሚሊኒየም(Millennium) = በእንግሊዘኛም ሆነ በላቲን ከሁለት የተቆራኙ ቃላት የተገኘ ቃል ነው:: እንደዚህ አይነት ጥምር ወይም ቁርኝት ቃላት ያላቸው ቋንቋዎች በእንግልዘኛ ቋንቋ Agglutinative languages ይባላሉ ስለዚህ በእንግሊዘኛ (Millennium) =(ሚል) ማለት ሺህ ሲሆን Annu (አነስ) ዓመት ማለት ነው::

በላቲን (Annus mirabilis) በእንግሊዘኛ Marvellous-Year ሲሆን ሁለቱም በአማርኛችን አስደናቂ አመት ማለት ነው::

ስለዚህ ይህንን የኢትዮጵያ ሁለት ሺህ አመት አስደናቂ አመት በዘመኑ ያለነው ትውልድ ለመቀበል ተቃርበናል:: እኛም በሳንዲያጎ ከተማ ነዋሪ የሆን ኢትዮጵያውያን ይህንን አስደናቂ ታላቅ አመት ክብረ-በአል አብረን ለማክበር እንዘጋጅ::

በየአመቱ መስከረም 1 ቀን በነጮች ( September 11) አዲሱን የኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ቀን ቅዱስ ዩሀንስ ወይም እንቁጣጣሽ እያለ በማክበር ለሁለት ሺህ አመት የደረሰ የኢትዮጵያ ህዝብ እነሆ ዛሬ በኪነ-ጥበባት በተዋቡና በተገነቡ በረጅም ዘመን ሂደት ውስጥ በአለፉ መሰረታዊና ስርአታዊ በሆነ በተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦቿ ባህል ትስስርና ህብር የዳበረ የባህል እድገትና ማህበራዊ ግንዛቤ ውጤት የሆነውን 2ሺ አመት አውደ-በአል ለመቀበልና ለማክበር የሁሉም ኢትዮጵያዊ ትብብርና ርብርብን አሳድጎታል:: ስለዚህ ኢትዮጵያውያን ባሉበት ሁሉ ኢትዮጵያዊ ታሪክ፣ ባህልና ወግ-ማዕረግ ይኖራል::

5 ኛው ገፅ ዞሯል


# ቀይ ባህር ምግብ ቤት

**Red Sea Restaurant**
**4717 University Ave**
**San Diego, CA 92105**
**Phone (619) 285-9722**

ምግባችን ለመሰንበት ሳይሆን ለመኖር የሚበላ ነው፡፡






# ሀረር ምግብ ቤት

The Best place to experience Ethiopian Food

**Takeout and Catering**

የሚልንዬም በዓልን ምክንያት በማድረግ

ሳምቡሳ በነፃ እንድሳለን፡፡

(619) 295-3735

2432 El Cajon Blvd,

San Diego, CA 92116

## <u>ለመዝናኛ</u>

(ይህ ክፍል የተለያዩ አጠር ያሉ ግጥሞች፤መጣጥፎች፤ አባባሎች፤ስነ ቃሎች፤ቀልዶች የሚቀርቡበት አምድ ነው)

### <u>የሰው ልክ</u>

የሰው ልጅ ሁለት መደብ አለው

አንደኛ: የጨቀየ ገላ አድፎ የተ ጣለው

የመንፃት ተስፋ ያለው፤

ሁለተኛ: እድፍ ሆኖ ሳለ እንዶድ ነኝ የሚለው::

(በእውቀቱ ስዩም 1998 :44)

ፅድቅና ኩነኔ ቢኖርም ባይኖርም

ከክፋት ደግነት ሳይሻል አይቀርም

(መንግስቱ ለማ-ኢብራሂም ካነበብኩት)

### <u>እስኪጣራ ማን ይጉላላል?</u>

አንዴ ዝሆን ግንድ ፍለጋ ሲዞር ጥንቸል ልቧ እስኪጠፋ እየሮጠች ስትገላመጥ ያያል:: ደንግጦ

«ምነው ምን መጣ ጥንቸል?» ብሎ ይጠይቃታል::

«አይ ወዲህ ነው ትልና» አሁንም ትጨናነቃለች::

ዝሆን አጥብቆ ይጠይቃታል ስለምን መሸበሯ

«አይ አንበሳ ይገደል ተብሎ እየታደነ ስለሆነ ለማምለጥ ነው»

ዝሆን በሳቅ ፈረሰና

«ታዲያ አንችን ምን አስፈራሽ?» ይላታል

«አይ እስኪጣራ ድረስ ማን ይጉላላል ብዬ ነው::» ብላው እርፍ :: አንበሳ እንዳትመስላቸው::

### <u>ያሳደግሁት ግመል ነከሰኝ  አትልምን?</u>

በድሮ ጊዜ እስልምና መስፋፋት በጀመረበት ጊዜ አንድ ሙእሚን (ሙስሊም) የወለደው ልጅ ቀጣፊ፤ሌባ፤ወሮበላ ይሆንበትና ይቸገራል:: በወቅቱ ችግር ሲኖር ለነቢዩ ሙሃመድ (ሰዓወ) ማማከር ደንብ ነበርና ሰውየው ለነቢዩ (ሰዓወ) «ይኽ ልጅ አስቸገረኝ እኮ» ይላቸዋል

«ምን አደረገ?» ይሉታል

«ይሰርቃል፤ይቀጥፋል፤ይዘርፋል...» ይመልሳል ሰውየው «ቆይ አንዴ» አሉና ነብዩ

«ለመሆኑ ቁርአን አስተምረኸዋል?» ይሉታል

«የለም አልቀራም» ይመልሳል ሰውየው

«የአገር ልማድ፤ባህል አስተም ረኸዋል?» ብለው እንደገና ይጠይቁታል::

«የለም አላስተማርኩም» ይመልሳል ሰውየው

«ታዲያ ልጄ አስቸገረኝ ለምን ትላለህ ያሳደግሁት ግመል ነከሰኝ አትልም::» ብለው መለሱለት አሉ::

(ያልዘሩት ይበቅላልን?)

(ኢብራሒም ከማስታውሰው)




Design by www.yebbo.com